ለኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስቴር
ዶ/ር አብይ አህመድ
አዲስ አበባ

ሰኔ ፲፭ ቀን ፳፻፲፩ ዓም በአማራ ክልል ርዕሰ መስተዳደር ዶ/ር አምባቸው መኮንን የክልሉ ጠቅላይ አቃቢ ሕግ አቶ ምግባሩ ከበደና የርዕሰ መስተዳደሩ የአደረጃጀት ዘርፍ አማካሪ አቶ እዘዝ ዋሴ እንዲሁም በኢፌዴሪ  መከላከያ ሠራዊት ኢታማዦር ሹም ጄኔራል ሳዕረ መኮንን እና ሜጀር ጄኔራል ገዓዚ አበራ ላይ የደረሰው አሰቃቂ ግድያም ሆነ ፣ መንግሥት ጥቃቱን አቀነባብረዋል ብሎ የጠረጠራቸው የብርጋዴር ጄኔራል አሳምነው ጽጌ ሞት ፣ ከጥቃቱ ጋር ተያይዞ በነበረው የተኩስ ልውውጥ መስዋዕት የሆኑት የፀጥታ አካላት ሕይወት ማለፍም እጅግ አሳዝኖናል ። በዚህ ጥቃት ለሞቱት ወገኖቻችን ቤተሰቦች ፤ ዘመዶች ፤ የሥራ ባልደረቦቻቸውና ጓደኞቻቸው ፤ ለአማራ ክልል ሕዝብ ብሎም ለመላው የኢትዮጵያ ሕዝብ መፅናናትን እንመኛለን ።

ሆኖም የደረሰው ጥቃት በመንግሥት እንደተገለፀው “የመፈንቅለ መንግሥት “ ሙከራ ተካሂዷል የሚለውን ፍረጃ ለመቀበል እንቸገራለን ። ምክንያቱም “መፈንቅለ መንግሥት” የሚመስሉ ሁኔታዎች ካለመታየታቸው ባሻገር ጥቃቱ ከደረሰ በኋላ በፌዴራል መንግሥትና በአማራ ክልል አመራሮች የተሰጡትና በመሰጠት ላይ ያሉት መረጃዎች የተዘበራረቁ ከመሆናቸው ባሻገር እርስ በርሳቸው የሚጋጩ ሆነው በመገኘታቸውና ለማመንም የሚያስቸግሩ በመሆናቸው ነው ።

የእነኚህ ከፍተኛ የሆኑ የአማራ ክልል አመራርና የፀጥታ አካላት እንዲሁም የሀገሪቱ ከፈተኛ የጦር መኮንኖች ግድያ ጅምላ እስራትና ወከባ ብዙ መዘዝ የሚያስከትሉና ያሀገራችንን ሕዝብ አብሮነት አደጋ ላይ የሚጥሉ የኢትዮጵያን ሀገራዊ አንድነት የሚፈታተኑ እንዲሁም ለዓመታት በዘለቀ የሕዝብ መራራ ትግል ያመጣውን የለውጥ ሂደት መስቀለኛ መንገድ ላይ የሚያስቀምጡ በመሆናቸው መንግሥት ለዚህ አደገኛ ክስተት ከፍተኛ ትኩረት በመስጠት በፈጠነ ሁኔታ ማስተዋልና ጥበብ በተመላበት አካሄድ መፍትሄ ሊያስገኝለት ይገባዋል ብለን በፅኑ ስለምናምን ከዚህ በታች ለሚከተሉት ጥያቄዎች አፋጣኝ ምላሽ እንዲሰጥ አጥብቀን እንጠይቃለን ።

፩ኛ/ ሰኔ ፲፭ ቀን ፳፻፲፩ ዓም የአማራ ክልል አመራሮች የፀጥታ አካላትና የኤፌድሪ ከፍተኛ የጦር መኮንኖች ግድያ በማን ተቀነባበረ ፣ እንዴት ፣ መቼና በማን ተፈፀመ የሚሉት ጥያቄዎች ነፃና ገለልተኛ የሆነ አጣሪ ኮሚቴ ወይም ኮሚሽን ተቋቁሞ በነፃነት ምርመራውን እንዲያካሂድ መንግሥት አስፈላጊውን ሁሉ እንዲያመቻችለት እንዲሁም አጣሪ ኮሚሽኑ የደረሰበትን የምርመራ ውጤት ለሕዝብ በይፋ እንዲያቀርብ ።

፪ኛ/ ገለልተኛ አጣሪ ኮሚሽኑ መርምሮና አጣርቶ ሪፖርቱን እስኪያቀርብ ድረስ መንግሥት “መፈንቅለ መንግሥት” ተሞከረ ወይንም ተካሄደ የሚለውን የራሱን ድምዳሜ ለማሳመን ከሚያደርገው ፕሮፓጋንዳ መሰል ቅስቀሳና አንድ ወገንን የመወንጀል ጥረት እንዲቆጠብ ።

፫ኛ/ በክልሉ አመራሮች ላይ የደረሰውን ጥቃት ተከትሎ በአማራ ክልል የተሰማራው የመከላከያ ሠራዊትና የፌዴራል የፀጥታ ቡድን እያደረሰ ያለውን የግድያ የጅምላ እስርና ማዋከብ እንዲያቆም ፤ ብሎም ክልሉን ለቆ በአስቸኳይ እንዲወጣ ።
፬ኛ/ ሰኔ ፲፭ ቀን ፳፻፲፩ የደረሰውን ጥቃት መንግሥት “መፈንቅለ መንግሥት” ብሎ ለሚጠራው ክስተት ፤ ተሳትፎ ሊኖራቸው ይችላል በሚል ሰበብ ወይንም ከክስተቱ ጋር በማያያዝ ለእስር የዳረጋቸውን ፤
ሀ/ የአማራ ብሄራዊ ንቅናቄ (አብን) አመራሮችና አባላት እንዲሁም ደጋፊዎች ፣ በተለይም
ለ/ በቁጥጥር ስር የዋሉ የጦር መኮንኖች ፤ ብርጋዴር ጄነራል ተፈራ ማሞና ኮሎኔአል አለበል አማረ ፣
ሐ/ የአዲስ አበባ ከተማ ባለአደራ ምክር ቤት አመራሮችና አባላት እንዲሁም ደጋፊዎች ፣
መ/ አቶ ማስተዋል አረጋ በቅርቡ በገቢዎችና ጉምሩክ መስሪያ ቤት ውስጥ የአመራሮችና ቁልፍ የሥራ ቦታዎች ላይ የተደረገው ምደባ በአንድ ብሄር አድሎአዊነት ላይ የተመሰረተ ነው ብሎ ለማኅበራዊ መገናኛ በማጋለጡ ፣
ሠ/ ጋዜጠኞች ፣
ረ/ ጥቃቱን ሰበብ በማድረግ ለጅምላ እስር የተዳረጉ ንፁሀን ዜጎች ፣

ያለ ምንም ቅድመ ሁኔታ በአስቸኳይ እንዲፈቱ  ።

፭ኛ/ በተለያዩ የኢትዮጵያ ክልሎች በንፁሀን አማሮች ላይ የተጀመረው ውንጀላም ሆነ የእስር ዘመቻ እንዲቆምና የታሰሩትም እንዲፈቱ ፣

፮ኛ/ ጥቃት ከደረሰ በኋላ በአማራ ክልል በተለያዩ ቦታዎች በመከላከያ ኃይሉና በፌዴራል የፀጥታ አካላት አማካይነት በጅምላ የተገደሉት ዜጎች የስም ዝርዝርና በምን ሁኔታ እንደተገደሉ ተጣርቶ ወንጀለኞችና የወንጀሉ ተባባሪዎች ለሕግ እንዲቀርቡና ለህዝብም ይፋ እንዲሆን ።

፯ኛ/ ከመደበኛ የፀጥታ አስከባሪው አካላት በተጨማሪ የተደራጁ በየክልሉ የሚገኙ የልዩ ኃይልና የሚሊሺያ አካላት መኖር እንደሌለባቸው በአብዛኛው የኢትዮጵያ ሕዝብ የሚታመንበት ሲሆን ፤ ነገር ግን በሁሉም ክልሎች በተመሳሳይ ጊዜና መንገድ መከናወን ያለበት ሆኖ እያለ ፤ በአማራው ክልል ብቻ በአሁኑ ሰዓት የተጀመረው የልዩ ኃይሉና ከቁሮ ጋር የለውጡ ሞተር ተብሎ ከሕዝብና ከከፍተኛ የመንግሥት አመራሮች እውቅና የተቸረው የፋኖ ታጣቂ ፣ ቤተሰቡንና ንብረቱን ለመጠበቅ በገዛ ገንዘቡ ገዝቶ የታጠቀውን ገበሬ ትጥቅ የማስፈታቱ እርምጃ በፍፁም ተቀባይነት የሌለው አድሏዊና አንዱን ወገን አጥቂ ሌላውን ተጠቂ ለማድረግ በታሰበ መልኩ የተቀነባበረ ስለሚመስል በአስቸኳይ እንዲቆም ።

፰ኛ/ የአማራ ክልል ሕዝብ በአንድነት ቆሞ እየደረሰበት ካለው ከፍተኛ አደጋ እንዳያገግም ፤ ብሎም እንዲዳከም ሕዝቡን ለመከፋፈል በመንግሥትና እንዲሁም ባንዳንድ አማራ ጠል በሆኑ ፖለቲከኞችና የግል መገናኛ አውታሮች የሚደረጉ ማናቸውም ሥውርና ግልፅ ዘመቻዎች በአስቸኳይ እንዲቆሙ ።

፱ኛ/ የአማራ ክልል አመራርና በክልሉ ያሉ ተፎካካሪ ፓርቲዎችን ለማዳከምና እንዳይጠናከሩ ለማድረግ የፌዴራል መንግሥት እያደረሰባቸው ካለው ዘርፈ ብዙ ተፅዕኖ እንዲገታ ።

፲ኛ/ ሰኔ ፲፭ ቀን የደረሰውን ጥቃት ተከትሎ የአማራውን ሕዝብ ታሪክ እንዲሁም አሁን የሚገኝበትን ቁመና ጭራሽ በማይገልፅ መልኩ ገፅታውን የሚያጠለሽ በሀገር ውስጥ ባሉ አማራ ጠል ኃይሎችና ዓለም አቀፍ እውቅና ባላቸው ሰዎች በተለይም ኢትዮጵያ አሁን ወደተቀረቀረችበት የጎሳ ፌዴራሊዝም እንድትወድቅ ሜዳውን ያመቻቹ የውጭ መንግሥት ወኪሎች አማካይነት የፕሮፖጋንዳ ዘመቻ እየተሞከረ ስለሆነ መንግሥት ተገቢውን ትኩረት ሰጥቶ እንዲከላከል ።

፲፩ኛ/ ሰኔ ፲፭ በከፍተኛ ባለስልጣናት ላይ የደረሰውን ጥቃት ሰበብ በማድረግ ሕዝቡ አማራጭ የዜና መገናኛ ተጠቅሞ ትክክለኛ መረጃ እንዳያገኝ መንግሥት የኢንተርኔትንና ማህበራዊ መገናኛ በተለይም ፌስ ቡክ ፤ ቴክስት አገልግሎት ሙሉ በሙሉ መዝጋቱና ብሎም መገደቡን አጥብቀን እንቃወማለን ። ይህ ድርጊት የኢትዮጵያን ሕዝብ የመናገርና የመፃፍ መብት በጅጉ ከሚገድቡ በአዓለም ላይ ካሉ ሶስት አገሮች ውስጥ ኢትዮጵያ አንዷ እንድትሆን አድርጓታል ። አሁንም የኢንተርኔት አገልግሎት ገደብ የተጣለባቸው አካባቢዎች ስላሉ ገደቡ በአፋጣኝ እንዲነሳላቸው ።

ከዚህ ጋር በማያያዝ ልናነሣ የምንፈልገው ፣ የዚህ ሁሉ ጠንቅና ቀውስ መነሻም ሆነ መሠረቱ የሀገሪቱ ሕገ መንግሥቱና እሱንም ተንተርሶ የተዋቀረው ነዋሪውን አንዱን የመሬቱ ባለቤት ፣ ሌላውን ባይታወር በማድረግ ፣ ለብዙ ሕዝብ ከቀዬው የመፈናቀል ፣ በግፍ የመገደል ምክን ያት የሆነው ፣ የጎሣ ተኮር ክልላዊ አስተዳደርና ስርአት ነው ተብሎ በአብዛኛው ዘንድ ይታመናል ። ችግሩ የበለጠ እንዲወሳሰብ ፣ ሕዝብ ርስበርሱ እንዲጋጭና እንዲተላለቅ ፣ በአገሪቷም ሰላምና ርጋታ እንዳይሰፍን ካልተፈለገ በስተቀር ፣ የሕዝቡን እኩልነት ነፃነትና አንድነት በሚያረጋግጥ በኢትዮጵያዊ ዜግነት ላይ የተመሰረተ ሕግ ማርቀቅና አስተዳደር ማቋቋም በአስቸኳይ እንዲታሰብበትና ለዚህም አስፈላጊው ርምጃና ዝግጅት እንዲደረግ በአጽንዖት እንጠይቃለን ።

ለነዚህ ከላይ ላስቀመጥናቸውና ለሌሎችም ተመሳሳይ አንገብጋቢ የሕዝብ ጥያቄዎችን መንግሥት ትኩረት ሰጥቶ አፋጣኝና ተገቢ ምላሽ የማይሰጥባቸው ከሆነ ሁናቴው የኢትዮጵያን ሀገራዊ አንድነት አደጋ ላይ የሚጥል ብቻ ሳይሆን መላው የኢትዮጵያ ሕዝብና ወዳጆቹ ከፍተኛ ተስፋ የጣሉበት የለውጥ ሂደት በእንደነዚህ መሰል ድርጊቶችና ክሥተቶች የተነሳ የመቀልበስ አደጋውን ከፍተኛ ስለሚያደርገው መንግሥት በጥንቃቄ ሊያያቸውና አስቸኳይ መፍትሄ ሊሰጥባቸው ይገባል ። በተለይም ጥቃቱ በኋላ መንግሥት እየወሰዳቸው ያሉት የኃይል እርምጃዎች ፤ ግድያዎች ፣ ወከባዎችና የጅምላ እስሮች ሕግን ለማስከበርና በወንጀል የተጠረጠሩትን ወደ ፍትሳ አካላት የማቅረብ ሂደት ሳይሆን የፖለቲካ ተቀናቃኝ ብሎ የፈረጃቸውን በሰበቡ የማዳከም የማሸስመድመድ አንገት የማስደፋትና የማጥቃት ድርጊቶች ይመስላሉ ። ይህ አካሄድ በፍጹም ተቀባይነት የሌለው ከመሆኑም ባሻገር ፣ አገራዊ አንድነታችንን የሚያናጋና ፣ የለውጡን ሂደት በከፍተኛ ደረጃ የደገፈውን ሕዝብ በተቃዋሚነት እንዲቆም የሚያነሳሳ ስለሆነ ፣ ይህንን ስጋት ለመቀነስም ሆነ ለማስወገድ ይረዳል ብለን ስለምናምን ፣ ከላይ ላቀረብናቸው ጥያቄዎች አስቸኳይ መልስ እንዲሰጣቸው በአጽንዖት እናሳስባለን ።

ለማጠቃለል ያህል ፣ እርስዎ በጠቅላይ ሚኒስቴርነት የሚመሩት የኢትዮጵያ መንግሥት ከላይ ለዘረዘርናቸው ጥያቄዎቻችን ምላሽ እንደሚሰጥና ፣ አስፈላጊ እርምጃዎችን እንደሚወስድ ፣ አለጥርጥር እየተማመንን ፣ እኛም በበኩላችን የኢትዮጵያን ህልውና በሚያስጠብቅና በተገቢው መንገድ ለማስቀጠል ለሚያደርጉት ጥረት ሁሉ ሙያዊ ድጋፋችንን ለመስጠት ዝግጁ መሆናችንን በአክብሮት እንገልፃን ።

፩. ፕሮፌሰር ኃይሌ ላሬቦ
፪. ዶ/ር ጋሻው ለቀ
፫.ዶ/ር ነጋሽ አምሳሉ
፬. ዶ/ር ጌታቸው በላይነህ
፭. አቶ ጌታቸው በጋሻው
፮.ዶ/ር ይግም ብሩ
፯. ዶ/ር ዓለማየሁ ዳዲ
፰. አቶ አራጋው ከፈለኝ
፱. ኢንጂነር ተክለ ሥላሴ ኃብተ ሥላሴ
፲. አቶ ይትባረክ ኃይሉ
፲፩. ኢንጂነር ዘላለም ተመስጌን
፲፪. ዶ/ር ተሾመ ፈረደ
፲፫. አቶ ቃለአብ ካሳሁን
፲፬. ወ/ሮ ጽጌረዳ ሙሉጌታ
፲፭. አቶ ተረፈ መኩሪያ
፲፮. ዶ/ር ሺፈራው ገሠሠ

ግልባጭ ፡-

ለኢ.ፌዴሪ ምክትል ጠቅላይ ሚኒስቴር አቶ ደመቀ መኮንን
አዲስ አበባ

ለኢ.ፌዴሪ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አፈ ጉባኤ
አቶ ታገሰ ጫፎ

ለኢትዮጵያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዘዳንት
ወ/ሮ መአዛ አሸናፊ

ለኢትዮጵያ ሰብአዊ መብት ኮሚሽን ኮሚሽነር
ዶ/ር ዳንኤል በቀለ

ለአማራ ክልላዊ መንግሥት ተጠባባቂ ርዕሰ መስተዳደር
አቶ ላቀ አያሌው
ባሕርዳር

በአሜሪካ የኢትዮጵያ አምባሰደር
አቶ ፍጹም አረጋ
ዋሽንግተን ዲሲ

ለሰብአዊ መብት ጉባኤ
አቶ ቢኒያም አባተ
አዲስ አበባ

ለኢትዮጵያ ሰብአዊ መብት ማኅበር ዋና ዳይሬክተር
አቶ ያሬድ ኃይለማርያም
ብረሰልስና ጄኔቫ